የሰ/መ/ቁ. 123123

ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

አይሸሹም መለሰ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ተኽሊት አፈወርቂ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን - የመቀሌ ቅርንጫፍ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የአመልካች ክስበ ይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጠውን ውሳኔ የህግ መሰረት ያለው መሆኑን በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው። ጉዳዩን እንደመረመርነው የአመልካች መኪና የኮንትሮባንድ ዕቃጭና ተገኝታለች በማለት ተጠሪ በቁጥጥር ስር ካዋላት በኋላ የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተለቅቃለች።

   አመልካች ተጠሪ መኪናዬን አላግባብ ቁጥጥር ስር በማዋል ጉዳት አድርሶብኛል በማለት ግንቦት 29 ቀን 2004 ዓ.ም የተጻፈ ክስ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ፣ በቀረበው ክስ ውስጥ ያሰፈረው ፍሬ ነገር ዕውነት ስለመሆኑ የአመልካች ጠበቃ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 92 መሰረት ለማረጋገጥ እንደማይቻልና አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 92 መሰረት የክሱን እውነተኛነት ቀርቦ ያረጋግጥልን በማለት በመቃወሙ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከጅምሩ በሬጅስትራር በኩል ቴክኒካል መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑ ተረጋግጦ ያልቀረበ መዝገብ ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገቡን ዘግቶታል።

2. ከዚህ በኋላ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረብኩት ክስ የተጋነነ ስለሆነ አስተካክዬ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ በማለት ጥቅምት 5 ቀን 2007 ዓ/ም አመልክቷል። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም አመልካች ስልጣን ላለው

ፍርድ ቤት ክስ ለማቅረብ እንደሚችሉ በመግለጽ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ጥር 4 ቀን 2007 ዓ.ም ለመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበ ሲሆን፣ ተጠሪ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ቴክኒካል ሁኔታዎችን ባለማሟላቱ የተዘጋ በመሆኑ ይርጋ ሊያቋርጥ አይችልም፡፡ ስለዚህ ክሱ በይርጋ ይቋረጣል በማለት ያቀረበውን መቃወሚያ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማለፉ፣ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የወሰነ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያለ ፍርድ ቤቱ ፈቃድ ክሱን ያቋረጠ በመሆኑ፤ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦት በነበረው ክስ ይርጋ አይቋረጥም፡፡ ስለዚህ መኪናዋ ከተለቀቀችበት ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንን በመቃወም ሲሆን ተጠሪም በጽሁፍ መልስ ሰጥቷል አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

3. ከስር የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው ሲሆን፣ በእኛ በኩል እንዳየነው አመልካች ተጠሪ መኪናዬን ከህግ አግባብ ውጭ በመያዝ፣ ጉዳት ስላደረሰብኝ ካሳ ይክፈለኝ በማለት በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 53029 ግንቦት 24 ቀን 2004 ዓ.ም አቅርቦት የነበረው ክስ በፍታሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት ህግ ቁጥር 92 መሰረት ዕውነት መሆኑ ተረጋግጦ ያልቀረበ መሆኑን በመግለጽ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክሱን ውድቅ በማድረግ መዝገቡን የዘጋው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በህጉ የተገለጸው ቴክኒካል መስፈርት አያሟላም ተብሎ የተዘጋበት መዝገብ እንዲንቀሳቀስለት ያመለከተው ፍርድ ቤቱ አልተሟላም ያለውን መስፈርት ለማሟላት ሳይሆን፣ በቀረበው ክስ የተገለጸው የገንዘብ መጠን የተጋነነ በመሆኑ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክሳችንን እንድናቀርብ በማለት እንደሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት ተረድተናል፡፡ ይህም አመልካች በተጠሪ ላይ በመዝገብ ቁጥር 53029 ግንቦት 24 ቀን 2004 ዓ.ም አቅርቦት የነበረው ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 278 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) በተደነገገው መሰረት የአመልካች ክስ በፍ/ስ/ስ/ህግቁጥር በተደነገገው መሰረት ዕውነት ስለመሆኑ ተረጋግጦ በከሳሽ (አመልካች) ባለመቅረቡ ምክንያት ውድቅ ያደረገው መሆኑንና አመልካች ጥቅምት 5 ቀን 2007 ዓ.ም ባቀረበው ማመልከቻ፣ በክሱ ውስጥ ተጠሪ (ተከሳሽ) እንዲከፍል የተጠየቀው ገንዘብ ዕውነትነት የሌለውና የተጋነነ መሆኑን የሚገልጽ በመሆኑ ከሳሽ ክሱን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 92 መሰረት ዕውነት መሆኑን በማረጋገጥ ክሱ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለማስቀጠል እንደማይችል መሆኑን በማረጋገጥ ክሱን ስልጣን ላለው ፍርድቤት ለማቅረብ እንዲችል ጥያቄ ያቀረበበት ነው፡፡

4. ይህም አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.ር92 መሰረት ዕውነት መሆኑን በማረጋገጥ ያቀረበው ክስ የሌለና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህ ቴክኒካል

ሁኔታ ካልተሟላ ጉዳዩን ልመለከተው አልችልም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.ር 278 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) መዝገቡ እንዲዘጋ የሰጠውን ትዕዛዝ ለማስለወጥ የሚያስችል በቂ ምክንያት በማቅረብ ክሱ እንዲቀጥል ያላደረገ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በመዝገብ ቁጥር 53029 ግንቦት 24 ቀን ያቀረበው ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.92 የተደነገገውን አስገዳጅ መስፈርት የማያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገብ እንዲዘጋ የሰጠው ትዕዛዝ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምንም አይነት ክስ እንዳላቀረበ የሚያስቆጥርና የይርጋ ጊዜ የማቋረጥ ውጤት የሌለው መሆኑን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.278 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) እና ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ይዘትና ይህ ሰበር ችሎት ስለድንጋጌዎቹ ዓላማ ተግባራዊ አፈጻጸምና ህጋዊ ውጤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 90361 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለመረዳት ይቻላል፡፡

5. ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች መኪናዋ እንድትለቀቅ በፍርድ ከተወሰነበት የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ለመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ እስካቀረበበት ጥር 5 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ፡፡ መብቱን ለማስከበር ህጋዊና ቴክኒካዊ መስፈርቶችን ያሟላ ክስ አቅርቦ እንደማያውቅ ተቆጥሮ የይርጋው ጊዜ መሰላት ያለበት በመሆኑ አመልካች የፍታሐ ብሔር ህግ ቁጥር 2143 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የሁለት ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ ከአስር ወራት በኋላ ክሱን ለመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ ከላይ የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 76156 መስከረም 5 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ